TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY

ዴሞክራሲዊ ምትሕብባር ትግራይ/ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር

የወገን መፈናቀል - የአምባገነኖች መሰሪነት

[ከትግራይ ዴሞክርሲያዊ ትብብር (ትዴት/ታንድ) የተሰጠ መግለጫ]

በቅድሚያ አምባገነኖቹ የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች በጉራ-ፈርዳ ነዋሪ ወገኖቻችን እያደረሱት ያለው ኢ-ሰብአዊ የማፈናቀል እርምጃ በጥብቅ እናወግዛለን። አያይዘንም የተፈናቀሉት ወገኖቻችን ያለምንም ሰባራ ምክንያት ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱና እስካሁን ለደረሰባቸው እንግልትና ኪሳራ ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፈላቸው አበክረን እንጠይቃለን።

ቀጥለን ይህ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው አሳዛኝ ድርጊት ጠለቅ ብለን እንድናየው የሚያስገድደን አንድ ዓብይ ምክንያት አለ፤ ይኸውም አምባገነኖቹ የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ይህ ዓይነት ጨካኝ እርምጃ ለመውሰድ የተነሱበትን መአዝን የሚመለከት ነው። በርግጥ በብዛት አማርኛ ተናጋሪ የሆኑት ኢትዮጵያውያን የጉራ-ፈርዳ ነዋሪ ወገኖቻችን እዛው ቦታ ለበርካታ ዓመታት ሰፍርው ሲኖሩ መንግስት ፈቅዶና አውቆ ለመሆኑ አስረጂ ሰነድ የመንግስት አካል በሆነው የወረዳው ጽ/ቤትና በተፈናቃይዎቹ ወገኖቻችን እጅ ይገኛል። ይህ ባይሆንስ፤ መንግስት አስተዳድረዋለሁ ለሚለው ህዝብ በሃገሩ ውስጥ ሰፈራ መሄድ የተገደደበትን ምክንያት አገናዝቦ አማራጭ መፍትሄ ያቀርብለታል እንጂ እንደጠላት ቆጥሮ የትም እንዲጣል ማስገደድ ነበረበትን ? የቤተ ክርስትያኑ መሪዎችስ ከጨካኙ መንግስት ጋር ወግነው አረሜናዊ ተግባር ላይ መሰማራት ነበረባቸውን ? ይህ አስከፊ ችግር በተናጠል የሚታይ ክስተት ሳይሆን ከአገዛዙ ባህርይና ከሚከተለው የአሰራር ዘይቤ ጋር ተያይዞ መቃኘት ይኖርበታል።

የችግሩ ማዕቀፍ የአምባገነኑ ቡድን ስልጣን ላይ አወጣጥና ስልጣን ከእጅ እንዳይወጣ የሚከተለው መሰሪ ስልት ያስከተለው መዘዝ ነው። በህዝብ አመኔታ ሳይሆን በጉልበቱ ስልጣን ላይ ገና ሲቆናጠጥ ጀምሮ ጸረ-ህዝብነቱን በይፋ ያረጋገጠበት፤ 140’000 (መቶ አርባ ሺ) ኢትዮጵያውያን ከኤርትራ ተፈናቅለው ሲባረሩ ህዝቡን በመካድ ለአፈናቃዩ ሻዕብያ ጥብቅና የቆመበት ሁኔታ እንገነዘባለን። አከታትሎም ህዝባዊ ጥያቄ አንግበው በሰላም ሰልፍ ለወጡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ይሁን በየወቅቱ አቤቱታ ለማሰማት አደባባይ በወጣው ህዝብ ላይ የጥይት ናዳ በመልቀቅ በጭካኔ መፍጀቱ ከዓይነ-ህሊናችን አልጠፋም። በጋምቤላ ህዝብ ላይ የተፈጸመው አስከፊ ጭፍጨፋና መጠነ-ሰፊ የህዝቡ መፈናቀል በድርጊቱ ተካፋይ የነበሩት መንግስታዊ ባለስልጣናት ሳይቀሩ በምሬት እያጋለጡት መሆኑ ይታወቃል። ይህ ዓይነት አረሜናዊ ድርጊት በመላው ሃገሪቱ (በትግራይ ርዕሰ-ከተማ በመቀሌም ጨምሮ) ተከስተዋል፤ ዋናው ነገር ከህወሓት/ኢህአዴጎች ስልጣን ላይ መቆየት ጋርም በቀጥታ የተሳሰረ ላሰራር በመሆኑ ክስተቱ መቀጠሉ ላይቀርም።

በጉራ-ፈርዳ የምናየው ወገንን የማፈናቀል እርምጃም ከማን-አህሎብኝነቱ አልፎ መሰሪ ተልእኮ ያዘለና እላይ ከተጠቀሱት ጸረ-ህዝብ ሽብርተኛ እርምጃዎች ተነጥለው መታየት የለባቸውም፤ እንደምንም ስልጣን ላይ መቆየት ብቻ ዓላማ ካደረገ ከአንድ ጥቅም ያስተሳሰረው ጠባብ ቡድን የሚፈልቁ የአሰራር ዘይቤዎች ናቸውና። ይህን መሰሪነት የተጠናወተው የከፋፍለህ-ግዛ ዘይቤን ለመስበር ከተፈለገም በተናጠል እንደማይሆን ላስቀድመን መገንዘብ ይኖርብናል። ተነጣጥሎ ለመመከት መሞከሩ እዛው-ቦዛው የመሰሪዎቹ ሰለባ ሆኖ መኖር ብቻ ነው የሚያስከትለው። እንዳው ባጭሩ፤ የተናጣል መፍትሄ በቅጡ ሲቃኝ ፍርሃትን ላነገሰው ሽብርተኛ አምባገነን ቡድን ይረዳል እንጂ መከራ ውስጥ ለተዘፈቀው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደማይበጅ እስኪበቃን ድረስ ተገንዝበናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በተናጠል እየተነሳ በተናጠል እየተመታ መኖር እንደማያዛልቀው ሁላችንም የምንገነዘበው ሃቅ ነው። በርግጥም የሚያዛልቀው ሁነኛው አማራጭ የናጠጡ አምባገነኖች አሸቀንጥረው እንደጣሉት እንደ ቱኒሶች፤ ግብጾች፤ የመኖች ተባብሮ፤ ተቀናጅቶ፤ በአንድ የጋራ ራዕይ ተመርቶ መነሳት ብቻ ነው። አምባገነኑ የህወሓት/ኢህአዴግ ቡድን እንደሆን ይህው የመጨረሻቸው ትንንቅ እንደማይቀርለት በሚገባ ያውቃል። ሰራዊት፤ ፖሊስ፤ ሰላይ፤ እስርቤት የማያግደው ማዕበላዊ ትንንቁም ወዴት እንደሚያመራ አላጣውም። ስለዚህም ነው ህዝቡ ተባብሮ እንዳይነሳበት ብሄረ-

ADDRESS: አድራሻ	P.O.BOX. 11340 Silver Spring. MD. 20913 USA	Dempo Str. 162 3029 CM. Rotterdam Netherlands	430 Wiggins Pr. App. No. 604 K1N-1A8, Ottawa- ONT. CANADA

ሰብ ከብሄረ-ሰብ፤ አንዱን የሃይማኖት ዘርፍ ከሌላኛው ሆን ብሎ ማናከስ እንደ ስልት የሚከተለው። ይህ ስልጣን ላይ የሚገኘው ቡድን በትግርኛ ተናጋሪው ህዝብ እንደተወከለ አስመስሎ በመስበክ (99.6% የኢትዮጵያ ህዝብ መርጦኛል እንደሚለው ሁሉ)፤ በሌላ በኩል ደግሞ ባጠቃላይ በአማርኛ ተናጋሪው ህዝብ ላይ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ በመቀስቀስና፤ በጉራ-ፈርዳ ማፈናቀል እንደምናየው ደግሞ የተናጠል መሰሪ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ የስርዓቱ ሰለባ የሆነው ህዝብ ሁሉ ቢያንስ ሆድና ጀርባ አልያም እርስበርሱ እየተናከሰ እንዲኖር በማድረግ ላይ እንደሚገኝ አይሳትም። መሰረተ-ቢስ ገንዘው ቡድን በህዝቦች ጥያቄ በተዋከበ ቁጥር ደግሞ ይችው መሰሪ ስልቱ እያጦፈ እንደሚቀጥባት ላንዴም መጠራጠር የለብንም።

የዚህ መሰሪ ስልት ጠንቅ ያልገባቸው ኣንዳንድ ወገኖቻችን አምባገነኖቹ ባቀናበሩት ጎሳዊ ወጥምድ ውስጥ ሰተት ብለው እየገቡ ህዝቡ እንዲተራመስና የአምባገነኖቹ የስልጣን ዘመን እንዲራዘም "ባለማወቅ" እየተተራመሱ ይታያሉ። የአምባገነኖቹ የአፈና መሳርያዎች በተባበረ የህዝብ ማዕበል ተሰባብረው ከጥቅም ውጭ እንዳይሆኑ አደናቃፊ አስተዋጻኦ እያ**ደረጉ** ናቸው። የፍትሕ ፈላጊው ህዝብ መሰረታዊ የአንድነት እሴቶችና ዘላቂ ጥቅሞች ስር እንዳይሰዱ አምባገነኖቹ ሲዘሩት ለኖሩት ጎሳዊ መርዝ ፍግ እየሆኑ ነው።

የህወሓት/ኢህአዴግ ቁንጮ መሪዎች መሰሪነት ከላይ በገለጽነው ማዕቀፍ (context) ውስጥ አስገብቶ ማየት ወደ ዘለቄታዊና ፈጣን መፍትሄ ሊያሸጋግረን እንደሚችል እሩቅ ሳንሄድ ከ66ቱ የኢትዮጵያው አብዮት፤ ፈንትው ብሎ ደግሞ ከቱኒስ፤ ግብጽና የመን የጋራ ንቅናቄዎች/ ህዝባዊ ማዕበሎች ብዙ ቁምነገር መቅሰም ይቻላል። ጸረ-አምባገነንነት ትግላችን በሃገራዊ አንድነትና ፍትሕ-ለሁሉም በሚል የወንድማማችነት ማዕቀፍ ካልታየ በስተቀር ማለቅያ ያጣው መከራችን አሁንም መሰሪዎቹ በቀድዱት ፈለግ እየተስፋፋና እርስበርስ እያጋጨ በየተራ ሊውጠን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል። በጋራ ራዕይና ትግል ከተጋፈጥነው ግን የአምባገነኖቹ ዕድሜ እንደሚያጥር ጥርጥር የለውም።

የጉራ-ፈርዳ ነዋሪ ወገኖቻችን መፈናቀል ማለቅያ ካጣው የመከራችን ፍሰት አንዱ አካል ነው። ኢ-ሰብአዊ ድርጊቱ ደግመን ደጋግመን ማውገዝ ብቻ ሳይሆን ዜጋዊ መብታቸው ተከብሮ ወደ ነበሩት ቦታ ከካሳ ጭምር እንዲመለሱ አጥብቀን ስንጠይቅ፤ ድሮውም ችግሩ የጋራ ነውና ለአጠቃላይ መፍትሄው በተናጠል ሳይሆን በጋራ እንነሳ እንላለን።

የአምባገነኖች መሰሪነት በተባበረ ክንድ ይከሸፋል!!
ኢትዮጵያ በዴሞክራት ልጆችዋ ትግል ትነሳለች!!

09.04.2012

ADDRESS: **P.O.BOX. 11340** **Dempo Str. 162** **430 Wiggins Pr. App. No. 604**
አድራሻ **Silver Spring. MD. 20913** **3029 CM. Rotterdam** **K1N-1A8, Ottawa- ONT.**
USA **Netherlands** **CANADA**